# ከአዲስ አበባ እስከ ጉባ

## ገብሬ ደ.

ትግራይ ኦንላይን - April 08, 2014 www.tigraionline.com



ገና መንጋቱ ነበር፡፡ አለቃዬ ደውሎ ወደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ተጉዤ ግንባታው የደረሰበትን ደረጃ እንድዘግብ ሲነግረኝ፡፡ ይሄኔ የተሰማኝ ስሜት ምን ብዬ ልንገራችሁ፡፡ ልዩ ነበር ማለት ነው የምችለው፡፡ ለምን ትሉ ይሆናል፡፡ ይህ ፕሮጀክት እኮ የድፍን ኢትዮጵያዊ ሞራል የገነባ፣ የድፍን ኢትዮጵያዊ ኪስ የዳበሰ፣ የሁሉም ዜጋ ልብ ያዋሃደ፣ ዜጎችን በአንድነት ያነቃነቀና የዘመናት የቁጭት ቁስላችንን የፈወሰ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ታሪካዊው ግድብ የእንችላለን ስሜታችንን ያደሰ፣ የዓለም ትኩረት የሳበና የሁሉም መገናኛ ብዙሃን ቀዳሚ አጀንዳ የሆነ ፕሮጀክት ነው፡፡ ለእኔ ይህ ግድብ የሃይል ማመንጫ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም የወኔ፣ የሃገር ፍቅር፣ የራዕይ፣ የኩራትና የአንድነት ስሜት ማመንጫም ጭምር እንጂ፡፡ በዚህ ፕሮጀክት መጀመር ግብፅ ድህነታችንን ተጠቅማ ለዘመናት ያደረሰችብን ውርደት ማብቂያ አግኝቷል፡፡ለዚህ ነበር ያችን የመሰረት ድንጋይ ሳኖር «የውርደት ካባችንን» ማራገፍ እንደጀመርን አስባለሁ ያሉት ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ፡፡

በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የሚደግፍም ሆነ የሚቃወም ሰው ሁሉ በአንድ ልብ የሚዘምርለት ፕሮጀክት ለመሆን የበቃውም ለዚህ ነው፡፡ ታድያ ይህን ብዙ የተወራለትና ገና ብዙ የሚባልለትን ግድብ በአካል ለማየት የማይጓጓ ማን አለ? የኔም ስሜት ይኸው ነበር፡፡ ከተጀመረ ጀምሮ አንድ ቀን በግሌ ሄጄ ለመጎብኘት ሳስብ ነበር ይህን እድል ያገኘሁት፡፡ እናም ተመስገን አልኩኝ፣ አሁን ምኞቴ ተሳካ፡፡ በዕለተ ዓርብ ከቀኑ ልክ 6:30 ላይ ከተመደበልኝ የካሜራ ባለሞያ ወንደሰን ጋር ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ደረስን፡፡ እቃችንን አስፈትሸን ገባንና በእንግዶች መጠባበቂያ ክፍል አርፈን የአሶሳውን በረራ መጠባበቅ ጀመርን፡፡ በሃሳብ ግን ያን ሁሉ ርቀት አቋርጬ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ደርሻለሁ፡፡ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በአእምሮዬ ሳልኩት፣ ደጋግሜም አሰብኩት፡፡ አከባቢውን፣ መልክዓምድሩን፣ ሰዉን፣ አየሩን፣ ውሃውን፣ ፕሮጀክቱን....በጉባ ሰማይ ስር ያለውን ነገር በሙሉ ለማየት ጓጓሁ፡፡ ግድቡ የሚገነባው ሁለት ተራሮችን በማገናኘት ነው የሚለው የመገናኛ ብዙሃን የዘወትር ዘገባ ደግሞ በአእምሮዬ ይመላለሳል፡፡ አንዱ ያጓጓኝ ነገርም ይሄ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማረፍያ በእንግዶች ማቆያ ስፍራ ላይ ነን፡፡ በረራችንን እየተጠበቅን፡፡ ስለ ህዳሴው ግድብ ማሰቤን አላቆምኩም፡፡ ይህን ታላቅ ስራ በአዕምሮዬ ስስለው ውስጤ በስሜት ይግላል፣ በሃሴት ይሞላል፣ በኩራት ይደምቃል፡፡ ለዚህ የዳረጉኝ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡በመጀመርያ ዓባይን

መገደብ ማለት ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በላይ የሃገራዊ ክብር መገለጫ ነው፡፡ ይህን ወንዝ መገደብ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት የህልም ዳቦ ተደርጎ ቆይቷል፡፡ አባይን ማልማት የማይደረስና የማይቻል እንደሆነ ተደርጎ እየታየ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሁወንዙን ሲያደንቀውና ሲዘምርለት፣ አልፎአልፎም ሲረግመውና ሲወቅሰው በርካታ ዘመናት ተቆጠሩ፡፡አገሪቱ የራሷን አቅም ገንብታ፤ የውጭሃይሎችን ተጽዕኖ ተቋቁማ  ይህን ተአምር ትሰራለች የሚል ቅንጣት ታክል እምነትም እሳቤም በማንኛውም አእምሮ ውስጥ አልነበረም፡፡

ዓባይን ላለመጠቀማችን በርካታምክንያቶች ቢኖሩም ዋናው ግን ለዘመናት የተዛመደን ድህነታችንነው፡፡ድሆች ናቸው አይችሉም ይሉናል፡፡ ድህነት ካለ ሁሉም ነገር የለም፡፡ ድህነት ሁሉንም ነገር ያሳጣል፣ በተለይ ደግሞ ሰብአዊ ክብርን፡፡ይህን ወንዝ ገድበን ለማልማት ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ገንዘቡን ማግኘት የሚቻለው ደግሞ በብድርና እርዳታ ነው፡፡ግብፅ ይህን ጠንቅቃ ታውቀዋለች፡፡ በዚህ ወንዝ መጠቀም ማለት ጠንካራ ኢትዮጵያን መፍጠር እንደሆነ ተገንዝባ አምስት ሳንቲም እንዳናገኝ በሩን ሁሉ ዘግታብናለች፡፡ከዚህ አልፋ በኢትዮጵያ ምድር ሰላምና መረጋጋት ከሰፈነ ይህች ታላቅ ሃገር ፊትዋን ወደልማት በማዞር ዳግም ልታንሰራራ ትችላለች ብላ በማሰብ ያች አረባዊት ሃገር ኢትዮጵያን የማዳከም ስልት ነድፋ ለዘመናት ተንቀሳቅሳለች፡፡እርስ በርሳችንን አባልታናለች፣ የውጭ ጠላቶችንም ትልክብናለች፣ የሰላም አየር እንዳንተነፍስና ለአፍታም ያህል ቀልባችንን አሰባስበን ብልፅግናን እንዳንመኝ አድርጋናለች፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተደማምረው ያከናነቡን የውርደት ካባና የፈጠሩብን የተስፋ መቁረጥ ስሜት እንዲሁ ቃላት የሚገልፁት ዓይነት አይደለም፡፡የህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት እንግዲህ ይህን ሁሉ የሸንፈት መንፈስን ነው ድል የመታው፡፡ አባይን የመገደብ ትርጉም ሰፊየሚሆነውም ለዚህነው፡፡ግድቡ የእንችላለን ስሜታችንን አለምልሞታል፣ ያጎናፀፈን የአእምሮ እርካታና የፈነጠቀው የእድገትተስፋቢናገሩት አያልቅም፡፡ይህን ሳስብ የሚሰማኝ ብሄራዊ ኩራት ሁሌም ውስጤ ይናኛል፡፡ስሜቱ በሁሉም ዘንድ አንድ ነው፡፡ ይህ ስሜትም ነው በግድቡ ዙርያ በአንድነት ያሰለፈን፡፡ ‹‹በእናታቸው ማህፀን ካሉትና ከተቀበሩት ሙታን›› በስተቀር በአባይ ጉዳይ ላይ የማይሳተፍ ኢትዮጵያዊ የለም ብለዋል አንዱ ጳጳስ፡፡ ተሳትፎው በጉልበትም፣ በዕውቀትም፣ በገንዘብም፣ በሃሳብም፣ በመንፈስም ነው፡፡

አሁንም በአውሮፕላን ማረፊያው የእንግዶች መጠባበቂያ ክፍል ውስጥ ነኝ፡፡ ስለዚህ ታላቅ ግድብ ዜና ልዘግብ ነው የምሄደው፡፡ ዜናውን በምን ጀምሬ በምን ልቋጨው የሚል ሃሳብም ብልጭ ይልብኛል፡፡ በመሃል ከጎኔ የተቀመጠው የካሜራ ባለሞያዬ ወንደሰን አናገረኝ፡፡ ‹‹ወይ የፈረንጅ ጥበብ፣ አሰበው እስቲ ይህን የሚያህል ግዙፍ ነገር ያውም ብዙ ህዝብ ተሸክሞ እንደቀላል ሰማይ ላይ ሲበር›› አለኝ፡፡ በየደቂቃው የሚነሱትንና የሚያርፉትን አውሮፕላኖች እየተመለከተ፡፡ እኔም አሰብኩ፣ በጣም ይገርማል፣ ወይ የፈረንጅ ጥበብ ማለቴ አልቀረም፡፡ ጨዋታችንን ሳንጨርስ የበረራ ሰዓታችን ደረሰና ጉዞ ወደ አሶሳ ሆነ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሰማይ ላይ ነን፡፡ አውሮፕላኑ መሬት ለቆ ወደ ሰማይ ሲፈተለክ ከጎኔ የተቀመጠው ወንዴ አማተበ፡፡ እኔም እንዲሁ የተቀደሰ ጉዞ አድርግልን ብዬ ፀለይኩኝ፡፡ በዚህ ሰዓት ሁሉም በየእምነቱ ከፈጣሪው ጋር እንደሚገናኝ እገምታለሁ፡፡ አሁን ሰማይ ላይ ነኝ፣ ፍርሃት ያዘኝ፣ ለጊዜው ስለ ህዳሴው ግድብ ማሰቤን አቆምኩ፡፡ ሁሌም ሰማይ ላይ ስሆን እሰጋለሁ፣ እፈራለሁ፣ ፈጣሪዬን የበለጠ አስበዋለሁ፣ ከማንኛውም ጊዜ በላይ አስበልጬ እፀልያሉ፡፡ ለነገሩ ሰማይ ላይ ሆኖ ይህን የማያደርግ ማን አለ፡፡ መፅሐፉ በጉርምስናህ ጊዜ ፈጣሪህን አስብ ቢለንም አብዛኞቻችን ግን ፈጣሪያችንን ይበልጥ የምናስበው በጭንቀታችን ወቅት ይመስለኛል፡፡

ለምን እንደሆነ አላውቅም፡፡ ሁሌም በምበርበት ጊዜ ያለፉትን አደጋዎች አስባቸዋለሁ፡፡ የኮሞሮሱን፣ የሊባኖሱን፣ የሎከር ቢውን፣ የማሌዥያውን.....ሌሎችም አሰቃቂ የሰማይ ላይ ክስተቶች ይመጡብኛል፡፡ የበረራ አስተናጋጇ ከፊት ለፊት ቆማለች፡፡ እንደተለመደው በአደጋ ጊዜ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ማስረዳት ጀመረች፡፡ እውነት ለመናገር ይህን ምክር ሁሉም ሰዉ በውል የሚገነዘበው አይመስለኝም፡፡ አንዳንዴ ይሄ የጥንቃቄ ትምህርት ምናለበት መሬት ላይ እያለን ቢሰጠን እላለሁ፡፡ ቀልባችንን አሰባስበን

በትኩረት እንሰማቸው ነበር፣ ያኔ ትምህርቱም ይገባናል፡፡ ሰማይ ላይ ሲኮን ግን ሃሳባችን ይበታተናል፣ ሊከሰት ስለሚችል አደጋ እያሰብን እንዴት ነው ያን ምክር የምንሰማው፡፡ የበረራ አስተናጋጇ ማብራሪያዋን ቀጠለች፡፡ «በአደጋ ጊዜ የመውጫ በሮች በግራና በቀኝ በኩል ይገኛሉ፣ የመተንፈሻ መሳሪያዎች ከላይ አሉላችሁ፣ የመንሳፈፊያ ቁሳቁሶች ከወንበሩ ስር ናቸው፣ አደጋ ሲከሰት ቅድሚያ ለህፃናት ስጡ.....» ትላለች፡፡ ይሄኔ አንድ ጓደኛዬ የሆነ ጊዜ አብረን ስንጓዝ የተናገው ነገር ትዝ አለኝ፡፡ «የአደጋ ጊዜ መውጫ በሮቹስ ይኑሩ፣ ግን ወዴት ነው የሚወጣው» ነበር ያለው፡፡ ምላሹ እንግዲህ ከሰማይ ወደ ሰማይ መሆኑ ነው፡፡

መንገድህን ሁሉ ለእግዚአብሄር አደራ ስጥ በሚለው የአሽከርካሪዎች ጥቅስ መሰረት መንገዴን ለፈጣሪ አደራ ሰጥቼ ለአፍታ ያህልስለ ሰማይ ላይ ጉዞዬ ማሰብ አቆምኩ፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መፅሄት ከፊት ለፊቴ ይታየኛል፡፡ ሰላምታ ባለፈው ዓመት በዓለም አሉ ከሚባሉ ምርጥ የበረራ መፅሔቶች አምስተኛው ሆኖ የተመዘገበ የህትመት ስራ ነው፡፡ ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ሰማይ ላይ መሆኔን ዘንግቼ መፅሄቱን ማገላበጥ ጀመርኩ፡፡ ስለ ከፋዎች የቡና ፍቅር የሚተርክ አንድ መሳጭ ፅሁፍ እያነበብኩ ከለምለሚ የአሶሳ ከተማ ደረስን፡፡ የበረራ አስተናጀጆቹ ተሰናበቱን፡፡ ከአውሮፕላኑ እየወረድኩ ስለሚቀጥለው መንገድ ማሰቤ ግን አልቀረም፡፡ ጓዛችንን ለመቀበል እየተዘጋጀን ሳለ በማላውቀው ስልክ ተደወለልኝ፡፡ «ደህና ዋልክ ገ/ሚካኤል፣ ስሜ'ው ነኝ፣ መኪና ልኬላችኋለሁ፣ ሾፌሩ ኢሳያስ ይባላል፣ በዚህ ስልክ ደውለህ አግኘው» ብሎ ተሰናበተኝ፡፡ በቴሌቪዥን መስኮት ሁሌ የማየው ያን ፂማሙን ሰውዬ አስታወስኩት፡፡ ኢንጅነር ስሜ'ው በቀለ፡፡ ምንኛ የታደለ ሰው ነው፣ በዚህ አዲስ ታሪክ በሚሰራበት ዘመንዋነኛው ተዋናይ ሆኗል፡፡ የሰማንያ አምስት ሚሊዮን ህዝብ ኪስ እና ልብ የዳበሰው የሰማንያ ቢሊዮን ብር ፕሮጀክት በሱ ጫንቃ ላይ ወድቋል፡፡ የአባይ የጡት አባት ይሉታል ብዙዎች፡፡ ይህን ሰው ሳስበው ግድቡን የማየት ጉጉቴ ይበልጥ ናረ፡፡

ሾፌራችን መጣ፣ አጋጣሚ ሆኖ ከዚህ በፊት አውቀዋለሁ፡፡ ከአሶሳ እስከ ጉባ ያለውን የማናውቀውን መንገድና ህዝብ እያስተዋወቀን ጉዞዎችንን ቀጠልን፡፡ ቀላል መንገድ እንዳይመስላችሁ፡፡ ከአሶሳ ከተማ 280 ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል፡፡ ከህዳሴው ግድብ ለመድረስ በአንድ ቀን ውስጥ ግማሹን በሰማይ፣ ገሚሱን በምድር ተያያዝነው፡፡ ከአሶሳ እስከ ሱዳን መገንጠያ ድረስ አስፋልት ሲሆን የሚበልጠው ግን የጠጠር መንገድ ነው፡፡ አቧራ አለ፣ ፀሃይ አለ፣ ሙቀት አለ፣ ድካምም እንዲሁ፡፡ አልፎ አልፎ ትናንሽ ከተሞችና መንደሮችን ስናቋርጥ ኢሳያስ መኪናውን በዝግታ ይነዳዋል፡፡ «የአከባቢው ሰዎች አቧራ ካቦነንከባቸው አይወዱም፡፡ ይህን አድርገህ ብታልፍ ከኋላ ተከትለው ወይም ስትመለስ አስቁመው ይፋረዱሃል፡፡ እነሱን ላለማስቆጣት በቀስታ መንዳት ነው የሚመረጠው» አለን፡፡ ይህ ተገቢ ነገር ነው፡፡

በኢሳያስ መኪና ውስይ ሆኜ የአሶሳን ምድር ግራ ቀኝ እቃኘው ጀመር፡፡ አከባቢው ለምለም ነው፡፡ ተፈጥሮ ባለችበት ማየትን ለሚናፍቅ የሸገር ሰው ይህ አከባቢ ገነት መባል ያንሰዋል፡፡ በረጃጅም ዛፎች፣ በሳርና ጫካ የተከበቡ የተበታተኑ ጎጆ ቤቶች ይታያሉ፣ የማንጎ ዛፎችም እንዲሁ፡፡ ያደኩበት አከባቢ የማንጎ ሃገር እንደሆነ ባውቅም መፈጠሪያው ግን እዚህ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የአሶሳ ማንጎ ልዩ ነው ሲባልም እሰማ ነበር፡፡ ይህ ተክል ለዚህ ምድርና ህዝብ ከተፈጥሮ የተቸረ ገፀ በረከት ነው፡፡ ሃብታቸው ግን እሱ ብቻ አይደለም፡፡ በሁሉም አቅጣጫዎች ለጥ ያለ ታራሽ መሬት ይታየኛል፣ የውሃ እጥረት እንደሌለም ልምላሜውይመሰክራል፡፡ እርሻም ሆነ አራሾች ግን አይታዩም፡፡ በዚህ አረንጓዴ ምድር በለም አፈር ተከቦ ድህነት እንደልቡ ተዝናንቶ እንደሚኖር መገመት አይከብድም፡፡

ነዋሪዎቹን ማስተዋል ጀመርኩኝ፡፡ ወንዶቹ እንደ ሱዳኖች ነጭ ጀለቢያ ያዘወትራሉ፣ ከላይ ደግሞ ነጭ ቆብ ይደርባሉ፡፡ አብዛኞቹ ሴቶች ሺቲ ለብሰዋል፡፡ በባህላዊ አለባበስ ያጌጡም ይታያሉ፡፡ አለባበሳቸው ከአከባቢው ሞቃታማ አየር ጋር የሚስማማ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከሱዳን ጋር የባህል መመሳሰል እንዳለ በግልፅ ያስታውቃል፡፡ ወንዶቹ ብዙውን ጊዜ በአህያ ተጭነው ነው የሚሄዱት፡፡ በዚህ አከባቢ አህያ

ፈረስንና በቅሎን ተክቶ ለሰው መጓጓዣነት ያገለግላል፡፡ ሴቶቹ ደግሞ አህያውን ተክተው ከአቅማቸው በላይ ተሸክመው ሲሄዱ ይታያሉ፡፡ አከባቢው አሁንም ድረስ የወንዶች ዓለም ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በጥቅሉ ለሴቶች የአበሳ ምድር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ወንዶቹ ምንም ዓይነት ስራ የሚሰሩ አይመስሉም፣ ሁሉም ነገር ለሴቶቹ የተተወ ነው፡፡ ይታያችሁ-በዚህ ዘመን አንዲት እናት በጀርባዋ ልጅ አዝላ፣ በሆዷ ሌላ አርግዛ፣ በራሷ ላይ እንጨት ተሸከማ፣ በሁለት እጆችዋ ደግሞ እቃ አንጠልጥላ ስትሄድ፡፡ በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ብዙ ነገር እየተሻሻለ ቢሆንም እዚህ ግን አሁንም በርካታ ስራዎች እንደሚቀሩ መገመት አያዳግትም፡፡

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ ጉባ ደረስን፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የከተመበት ስፍራ ነው፡፡ አከባቢው ሲታይ አንድ መለስተኛ ከተማ ነው የሚመስለው፡፡ በመብራት ደምቋል፣ በግንባታ እየተጣደፈ ነው፣ ወደ 1600 የሚሆኑ ማሽነሪዎች 24 ሰዓት ሙሉ ይንቀሳቀሱበታል፡፡ በርካታ ተሽከርካሪዎች ጠጠር ጭነው ከወዲያ ወዲህ ይርመሰመሳሉ፡፡ ትላልቅ ማሽነሪዎች እዛም እዚህም ቁፋሮውን ያፋጥኑታል፣ ግዙፍ የድንጋይ ወፍጮዎች የጠጠር ምርቱን ያጣድፉታል፡፡ ይህን ፕሮጀክት እውን ለማድረግ የተሰለፉት ወደ 5500 የሚሆኑት ሰራተኞች እረፍት የላቸውም፡፡ ሌተቀን ይሰራሉ፡፡ እዚህ ቦታ ሁሌም ህይወት አለ፣ በፍፁም አይመሽም፡፡ እድል ገጥሞት ላየው ሰው ሁሉ የተለየ ስሜት ነው የሚሰጠው፡፡ ከተማ ውስጥ ሆነን ከኪሳችን የሚወጣው ብር ምን እየተሰራበት ይሆን ብለን ስናስብ ምላሹን በቀላሉ ላንደርበት እንችላለን፡፡ እርግጥ ነው በመገናኛ ብዙሃን የምናየው ነገር አለ፡፡ ሆኖም ማየትን የሚያህል የለም፣ ማየት ማመን ብቻ ሳይሆን ማየት ለበለጠ ትጋት እንደሚያነሳሳ ይህን ግድብ ሄዶ ያየ ሁሉ ይመሰክራል፡፡ ለዚህ ፕሮጀክት ከዚህ በላይ ለማድረግም ያስመኛል፡፡

የፕሮጀክቱን ዋና ስራ አስኪያጅ አገኘነው፡፡ «ስመኘው እባላለሁ» ብሎ ተዋወቀን፣ እኛም ራሳችንን አስተዋወቅን፡፡ ፂማም፣ አጭር፣ ደንደን ያለ፣ ጠይም ሰው ነው፣ ጉርድ ሸሚዝ ለብሷል፣ ግርማ ሞገሱ ይገርማል፡፡ የበረሃ ሰው ነው፣ ከዚህ በፊት በበርካታ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ግንባታ ተሳትፏል፣ የግልገል ጊቤ ሁለት ደግሞ ስራ አስኪያጅ ነበር፡፡ ዛሬ ወደየቤታችን ደርሶ የምናየው ብርሃን የእሱ ላብ አለበት፡፡ የላቀ ሃገራዊና ህዝባዊ ስሜት ይስተዋልበታል፡፡ የተለየ ስብእና ባለቤት ነው፡፡ ሰርቶ የሚደክም አስቦ የሚሰለቸው አይመስልም፡፡ ቀኑን ሙሉ ሲሰራ ውሎ እኛም ስንደርስ ልረፍ አላለም፡፡ አንደበቱ ስለ ሃገሩና ህዝቦቹ ታላቅነት ይዘምራል፣ እውነት ከውስጡ ይፈልቃል፣ በስሜት ነው የሚናገረው፣ ቃላቱ ውስጤ ድረስ ሰርፀው ይገባሉ፡፡ «የኢትዮጵያ ህዝብ ብር፣ ወኔና ድጋፍ እንዲሁም የዘወትር ፀሎት ምን እየሰራ እንደሆነ ላስጎብኛችሁ፣ ይህ ግድብ ይህን ታላቅና ኩሩ ህዝብ ወደ ላቀ ታላቅነት ያደርሰዋል» ብሎን ወዲያዉኑ በመኪናው ይዞን መዞር ጀመረ፡፡ ኤንጂነሩ ለደህንነት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ የምንንቀሳቀሰው በግንባታ ስፍራ ውስጥ ስለሆነ በዛ ምሽት ሳይቀር ሄልሜትና የደህንነት ጃኬት አለበሰን፣ እናም ጉብኝታችንን በይፋ ጀመርነው፡፡

ወደ ዋናው ግድብ ከመሄዳችን በፊት አስቆመን፡፡ «እነዚህ ሁለት ፋብሪካዎች የጠጠር ማምረቻዎች ናቸው፣ ከግድቡ ግራና ቀኝ ነው የተገነቡት፡፡ በነዚህ ፋብሪካዎች የሚመረተውን ጠጠር በቀጥታ ወደ ግድቡ በመውሰድ የአርማታ ሙሌት ስራ ይከናወናል፡፡ ለዚህ ስራ የተዘረጉ ኮንቬያንስ ቤልትስ ወይም የጠጠር ማመላለሻ ቀበቶችም ተዘርግተዋል» አለን፡፡ ቀጥለን ወደ ግድቡ አመራን፡፡ ኤንጂነር ስመኘው ማብራራቱን ተያያዘው፡፡ «ስራው ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ እተፋጠነ ነው፡፡ ግድቡ የሚገነባው በአርማታ ሙሌት ሲሆን አሁን ቁፋሮው ተጠናቆ ሙሌቱ ተጀምሯል፡፡ ከዝቅተኛው ወለል ነው የተጀመረው፡፡ ይህ የአርማታ ሙሌት ስራ 1780 ሜትር ርዝመትና 145 ሜትር ቁመት ያለው የግድቡ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ ይቀጥላል፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ያሉት የሲቪልና የሃይድሮሜካኒካል ስራዎችም ሳሊኒ በተባለው የጣሊያን ኮንትራክተርና የኢትዮጵያው ኤንጂነሪንግና ብረታ ብረት ኮርፖሬሽን የጋራ ትብብርና ቅንጅት እየተከናወኑ ናቸው»፡፡ ለሃገር በቀሉ ኩባንያ ያለው አድናቆት ይገርማል፡፡ ሃገር ከጥገኝነት ተላቅቃ ዕድገቷን ያለምንም መሰናክል ማራመድ የምትችለው እንደ ብረታብረትና ኤንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የመሳሰሉ ዓቅም

ያላቸው የልማት ተቋማት ሲፈጠሩ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ደግሞ እንዲህ ዓይነቶቹ ሃገር በቀል ኮንትራክተሮች ልምድና እውቀት የሚያካብቱበት መሆን አለበት ይላል፡፡ቀጠለ ኤንጅነር ስመኘው፡፡ ‹‹በአሁኑ ጊዜ እንደምታዩት ወንዙ ቋሚ መንገዱን ትቶ በጊዜያዊነት በክፍት ቦይ እንዲፈስ ተደርጓል›› አለ፡፡ ይህ ወሳኝ የስራ ምዕራፍ በሚዲያዎች ይፋ በመደረጉ በግብፆች ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤና ቁጣ መቀስቀሱን አስታውሳለሁ፡፡እኔን የገረመኝ ግን ወንዙ እንደሚገደብ እያወቁ የውሃው መንገድ መቀያየር ለምን እንዳስደነገጣቸው ነው፡፡ ሊያስጨንቃቸው የሚገባው ነገር እኮ የወንዙ መንገድ መቀያየር ሳይሆን እነሱ ጋር የሚደርሰው የውሃ መጠን እንዳይቀንስ ነው፡፡ እንደዛ እንዳልሆነ ደግሞ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ውሃው ሃይል አመንጭቶ እነሱ ወደነሱ ይቀጥላል፡፡ ግድቡ የውሃ ድርሻቸውን በጎላ መልኩ እንደማይቀንሰው በተደጋጋሚ እየተነገራቸው ነው፡፡ ለዚህ ዋስትና ይሰጠን ብለው የሙጥኝ የሚሉት ነገር ግን አለ፡፡ አስገራሚው ነገር እኮ ይህ ዋስትና የሚሹለት የውሃ ድርሻ በ1959 ኢትዮጵያን አግልለው ከሱዳን ጋር ሲፈራረሙ ይገባናል ያሉት 55.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ነው፡፡ ቀሪውን 18.4 ቢሊዮን ደግሞ ለሱዳን ሰጥተዋታል፡፡ አስቡት እስቲ ከላይ ያሉት የወንዙ ምንጭ የሆኑ ሃገራት ምን ይጠጡ አይባልም? ይህን በፍፁም ማሰብ አይፈልጉም፡፡

ከአባይ ወንዝ ብቻችንን እንብላ የሚለው አባዜያቸው መቼም ቢሆን የሚለቃቸው አይመስለኝም፡፡ይህ የግብፆች አቋም ጠ/ሚ መለስ ዜናዊን በእጅጉ እንዳስገረማቸው አልፈዋል፡፡ ‹‹እንዴት ሰው ዝንተዓለምብቻዬን ልብ ላይላል›› በማለት ዘወትር ይጠይቁ ነበር፡፡ ‹‹እኛ የግብፅን ችግር የምንገነዘበውን ያህል እነሱም ይህች የ85 ሚሊዮን ህዝቦች መኖርያ የሆነች ሃገር ለ40 ዓመታት ያህል ረሃብ የነገሰባት መሆኗን መረዳት ይገባቸዋል፡፡ለዚህ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያቶች በቴሌቪዥን መስኮት ከሚያዩዋቸው የተራቡ ሰዎችም ስልበላይ ማስረጃ ልናቀርብላቸው አንችልም፡፡ እኛ እየበላን ኢትዮጵያውያኑ ይራቡ የሚለው አቋማቸው ስሜት አይሰጥም፡፡እኛም ከዓባይ ወንዝ መጠቀም እንዳለብን መገንዘብይገባቸዋል፡፡የአባይን ውሃ በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል የመፍትሄ ሃሳብ ያስፈልገናል፣‹ውሃው እንዳለ ለግብፅና ለሱዳን ብቻ ነው የሚገባው፣ ሌሎቹ የተፋሰሱ ሃገራት ድርሻ የላቸውም›የሚለው የተሳሳተ ሃሳባቸው ግን መቼም ቢሆን አያግባባንም፡፡ይህ ለዚህ ዘመን የማይመጥን የ19ኛው ምዕተ ዓመት አስተሳሰብ ነው›› ብለው ለግብፁ ቴሌቪዥን የነገሩትን አስታውሳለሁ፡፡

የህዳሴው ግድብ ጉብኝታችን አላበቃም፣ ገና ብዙ የምናያቸው ስራዎች አሉ፡፡ ዋናው ግድብ የሚሰራበት ቦታ ላይ ቆመናል፡፡ ኤንጂነሩም ማብራርያ እየሰጠን ነው፡፡ ‹‹አሁን ወንዙን በቋሚነት ለመጥለፍ የሚያስችሉ አራት የብረት አሸንዳዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የብረታ ብረትና ኤንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ነው እነዚህን መሳሪያዎች ያመረታቸው፡፡ ከቀናቶች በኋላ የተከላ ስራው ይጠናቀቅና ወንዙ ቋሚ መንገድ ይኖረዋል፡፡ በሁሉም የግንባታ ስራዎች ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የጥራት ፍተሻ እናከናውናለን›› አለ፡፡ በእስካሁኑ ክንውን በርካታ የግንባታ ምዕራፎች ታልፈዋል፡፡ የፕሮጀክቱ ዋነኛ አካላት የሆኑት የግድቡ፣ የሃይል ማመንጫ ጣቢያዎች፣ የሃይል መቆጣጠሪያ ማዕከልና የሃይል ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ ስራዎች ሁሉም በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በመቀላጠፍ ላይ ናቸው፡፡ በፕሮጀክቱ ዲዛይን  መሰረት ሲከናወኑ የነበሩ የተለያዩ የቁፋሮ ስራዎችምተጠናቀው የዋናው ግድብ ግንባታ ስራ ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ በዚህ ወቅት ከአጠቃላይ ስራው ሰላሳ ሁለት ከመቶ የተከናወነ ሲሆን በሚቀጥለው ዓመት የመጀመርያውን 750 ሜጋዋት ሃይል ማመንጨት ይጀምራል፡፡ ከእንግዲህ የሚከናወኑት ስራዎች የቀለሉና በፍጥነት የሚያልቁ ናቸው፡፡ አስቸጋሪው ጊዜ ከኋላችን ነው ያለው ብሎናል ኤንጂነር ስመኘው፡፡ የምሽቱ ጉብኝታችን በዚሁ ተጠናቀቀና ወደ ማረፊያችንም ተመለስን፡፡

ሁሌም የዚህን ታላቅ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ባየሁት ቁጥር ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ምን ብሎት ይሆን እያልኩኝ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ ኤንጂነሩን ሳገኘው ‹‹ለመጨረሻ ጊዜ ከመለስ ጋር የተገናኛችሁ ዕለት ምን ተባባላችሁ›› ብዬ ልጠይቀው ፈለግኩኝ፡፡ ግን ይሉኝታ የሚባለው ኢትዮጵያዊ ባህል ሸብቦ ያዘኝ፡፡ ሆኖም እራት እየበላን የሆነ ሰዓት ላይ ስለ መለስ አንስተን መጫወታችን አልቀረም፡፡

ኤንጂነሩ «አርአያችንን በድንገት አጣነው፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ ህይወቱን የሰጠ ጀግና ነው» አለኝ በከፍተኛ



ስሜት ተውጦ፣ በትካዜ ፈዞ፡፡ በታላቁ መሪ ህልፈት ውስጡ ምንኛ እንደቆሰለ ያስታውቃል፡፡ «እነ ማንዴላ፣ እነ ቸጎቬራ፣ እነ ሆቺሚኒ.....ከመለስ ጋር ሲነፃፀሩ እኮ ምንም አልሰሩም»በማለት ቀጠለ፡፡ ይሄኔ አንድ ነገር አስታወሰኝ፡፡ ቻርለስ አቡግሬ ስለ ታላቁ መሪ የፃፈው ማስታወሻ ነው፡፡ «መለስ እንደ ማንዴላ ዝነኛ ለመሆን ምን ያህል መጨነቅ ነበረበት፣ ምንስ ማድረግ ይገባው ነበር» ብሎ ይጠይቅና «መለስን ያስጨንቀው የነበረው ነገር እንደ ማንዴላ የመሆኑ ጉዳይ ሳይሆን ልማታዊ ሃሳቦቹና ፕሮግራሞቹ ምን ያህል በህዝብ ዘንድ ሰርፀው የህዝቦቹን ህይወት መለወጥ መቻላቸው ነው» የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡

የዝና መሰረቱ የተለያየ ነው፣ ሰዎች ዝነኛ ለመሆን የሚከተሉትም መንገድ ይለያያል፡፡ ጠ/ሚ መለስ አንድም ቀን ዝነኛ ልሁን የሚል አመለካከት አንፀባርቀው አያውቁም፡፡ ዓላማቸው ለኢትዮጵያ ህዳሴ መስዋዕት ሆኖ ማለፍ ነበር፣ አደረጉትም፡፡ ኤንጂነር ስመኘው ቀጠለ «እነሱ (እነ ማንዴላን ማለቱ ነው) ታግለው ህዝብን ከጦርነት ነፃ አውጥተው ይሆናል፡፡ መለስ ግን ያን ብቻ አይደለም ያደረገው፡፡ ይህን ታላቅ ህዝብና ሃገር ደርግን ከመሰለ ጨካኝ አውሬ ብቻ አይደለም የታደገው፡፡ የሰላም፣ የልማት፣ የአስተሳሰብና የፖለቲካ ነፃነትም አጎናፅፎታል፡፡ በዓለም መድረክ ህዝቡንና ሃገሩን ለማስጠራት በቅቷል፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ከዓለም መሪዎች ቀዳሚው ተጠቃሽና ተዋናይ ሆኖዋል፡፡ የነፃነት ታጋይ ብቻ ሳይሆን ቆራጥ መሪ፣ ተመራማሪ፣ ፀሃፊ፣ መምህርና ተንታኝ ነው፡፡ ህዝባችንን ባለራዕይ አድርጎታል፣ የሰው ልጅ በጥረቱ ድህነትን ከመሰለ ውርደት ነፃ መውጣት እንደሚችል በተግባር አሳይቶናል፡፡ ለእኔ ዜናዊ ዝንተዓለም ከሚዘመርላቸው ታላላቅ ሰዎች ሁሉ የላቀ ታላቅ ሰው ነው» ብሎ ታላቁን ሰው በምርጥ ቃላት ገለፀው፡፡ ይህ መሰሉን መሪ ነው ያጣነው አልኩኝ በውስጤ፡፡

ከኤንጂነሩ ጋር ጨዋታችንን ቀጠልን፣ የጀመረውን አርዕስት አልቋጨውም፣ የቀረበልኝን እራት እየበላው እሰማዋለሁ፡፡ መለስና ኤንጂኔሩ ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙ እለት ምን ተባብለው ይሆን የሚለው ጥያቄዬ አሁንም በአእምሮዬ ይመላለሳል፡፡ መልሱን ለመገመትም ይዳዳኛል፡፡ «ይህ ትልቅ ሃገራዊ ሃውልት በእጅህ ወድቋል፣ ለፍሬ ታበቃው ዘንድ በኢትዮጵያ ህዝብ ስም አደራ እልሃለው» ብሎት ይሆናል እላለሁ፡፡ ከሁለት ሰዓት የአብሮነት ቆይታችን በኋላ ግን የበለጠ እየተላመድንና እየተቀራረብን መጣን፡፡ ኤንጂነሩ አንዴ ከቀረቡት አይከብድም፣ ቀለል ያለና ሲበዛ ተግባቢ ነው፡፡ እናም አሁን የፈለኩትን ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ፡፡ «ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመጨረሻ ጊዜ መቼ ነው ያየሃቸው ኤንጂነር» ብዬ የመጀመሪያ ጥያቄዬን ሰነዘርኩ፡፡ ትንሽ እንደመተከዝ ብሎ ምላሹን ቀጠለ፡፡ «ያን ጊዜ ሳስታውሰው ውስጤ በእጅጉ ይረበሻል፣ ይገርመኛልም፡፡የግድቡ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ ነበር የተገናኘነው፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ የመሰረት ድንጋይ ሲያኖርም ሆነ የልማት ስራዎችን ሲመርቅ ጉዳዩን ጨርሶ በፍጥነት ነበር የሚሄደው፡፡ ያኔ ግን ባልተለመደ ሁኔታ በጣም ብዙ ቆየ፡፡ አሁን ሳስበው ተመልሶ እንደማይመጣ ውስጡ ነግሮት ይሆን እላለሁ፡፡ ለረዥም ሰዓት አወራን፣ አጃቢዎቹ ‹አረ እባክህ ሰውየው እኮ በሙቀት ነደደ ይሉኛል፣ የትኛው ሰውዬ እላቸዋለሁ፣ መለስ ነዋ ይሉኛል፡፡ ሆኖም መጫወታችንን ቀጠልን» አለኝ፡፡ የመኝታ ሰዓታችን ደርሶ ተለያየን፡፡ ከኤንጂነር ስመኘው ጋር የነበረኝ የምሽት ቆይታምበዚሁ አበቃ፡፡

በነገታው ዋናውን ቀረፃ ልናከናውን ነው፡፡ እናም ቁርሳችንን በልተን ወደ ስራ ተሰማራን፡፡ ከኢሳያስ ጋር ወደ አንዱ ከፍታ ሄደን የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ገፅታ ማሳየት በሚያስችል መልኩ ቀረፃችንን ጀመርን፡፡ አባይን ተንጋሎ አየሁት፣ ፀባይ ገዝቷል፣ «ገና አደብ ይገዛል» አልኩኝ በውስጤ፡፡ ይህኛው ቦታ ሃገሩን የሚሰናበትበት የመጨረሻው የመውጫ በር ነው፡፡ ታይቶ አይጠገብም፣ ወንዙ አንዳች ምትሃታዊ ሃይል እንዳለው ግርማ ሞገሱ ይመሰክራል፡፡ «የአባይ ውሃ ነው ፀበል፣ ከኢትዮጵያ ሃገሬ ይፈልቃል» የሚለው ዜማ ያቃጭልብኛል፡፡ "አባይበመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱትና ከገነት ከመነጨት አራት ወንዞች አንዱ ነው፡፡ ለኛና ግብጽን ለመሰሉ ሃገራት ህይወት ይሰጠናል" ብለው ገልፀውታል አባ ዳዊት ለአልጀዚራ ቴሌቪዥን ሲናገሩ፡፡ እውነታቸውን ነው፣ በተለያየ መልኩ ህይወት ይሰጣል፣ በተለይ ለኛ ግን ገና አሁን ነው የበለጠ ህይወት የሚሰጠን፡፡ እዚህ ቦታ ላይ የሚመነጨው 6000 ሜጋዋት ሃይል በኢትዮጵያ ምድር ብዙ ህይወት ይዘራል፡፡

ከከፍታው ላይ ሆኜ እነዛን ትይዩ ተራሮችም አየኋቸው፣ ግድቡ እነዚህን ሁለት ተራሮች በማገናኘት ነው የሚገነባው፡፡ ከግድቡ ጀርባ የጣናን ሃይቅ ሁለት እጥፍ የሚሆን ውሃ የመያዝ ዓቅም ያለው ግዙፍ ሰው ሰራሽ የውሃ አካል ይፈጠራል፡፡ ሃይቁ 246 ኪሎ ሜትር ርዝመት ይኖረዋል፡፡ ከአዲስ አበባ ደጀን ድረስ ያለው ርቀት እንደማለት ነው ብሎኛል ኤንጂነር ስመኘው፡፡ሰው ሰራሽ ሃይቁ ብዙ አገልግሎት ይሰጣል፣ በተለይ ለጀልባ ትራንስፖርት፣ ለዓሳ ምርት፣ ለቱሪዝም መስህብነት እንዲሁም የአከባቢውን የአየር ሁኔታ ከማስተካከል አኳያ፡፡ እዛው ኮረብታ ላይ ሆኜ በርካታ አውቶቡሶች ሲመጡ አያለሁ፡፡ ትናንሽ መኪኖችም ጭምር፡፡ ግድቡን ለመጎብኘት የመጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በአሁኑ ወቅት በሃገሪቱ ውስጥ አሉ ከሚባሉ መስህቦች አንዱ ለመሆን በቅቷል፡፡ ከተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በየቀኑ በርካታ ጎብኚዎች ይመጣሉ፡፡ ከወጣት እስከ አዛውንት፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ተማሪው፣ ሰራተኛው፣ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ፣ ምሁሩ፣ ወታደሩ.....ሁሉም እየመጣ ያየዋል፡፡ ከኪሱ የወጣው ገንዘብ ምን ተአምር እየሰራ እንደሆነም ይመለከታል፡፡

እዛ በዋልንበት ቀን ኤንጂነር ስመኘው በርካታ ጎብኚዎችን አስተናግዷል፡፡እንግዶቹን ከሚገመተው በላይ ያከብራል፡፡ «ጎብኚዎቻችንን በአግባቡ ተቀብሎ ማስተናገድ ከዋናው ስራችን እኩል እናየዋለን»ብሎኛል፡፡ ቀኑ እሁድ ስለነበር በርካታ ጎብኚዎች መጥተዋል፡፡ ኤንጂነሩም በወረፋ እንግዶቹን ተቀበለ፡፡ ከዚህ በኋላ ስለ እያንዳንዱ ነገር ገለፃ ማድረግ አለበት፡፡ «እዚህ የሚመጣው ሰው ሁሉ ስለ ግድቡ በቂ መረጃ ታጥቆ

መሄድ አለበት» ብሎ ያምናል፡፡ የሚናገረው ነገር ሁሉ ከዚህ ጠንካራ እምነቱ የመነጨ ነው፡፡ እንግዶቹ በክቧ ቤት ውስጥ ቦታቸውን ይዘው ተቀመጡ፡፡ ቆመው ገለፃውን ለመስማት የተዘጋጁም ነበሩ፡፡ ኤንጂነሩ እራሱን አስተዋውቆ ስለ ፕሮጀክቱ መናገር ጀመረ፡፡ *«የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሌም ከጎናችን ነው፣ ዓቅምና ጉልበት ሆኖናል፡፡ ይህ በአፍሪካ ትልቁ የሆነው ግድባችን የሃገራችንን የኢንዱስትሪ ሽግግር ሂደት እውን ያደርገዋል፡፡ ታላቁ መሪ ያሳዩንን የታላቅነት መንገድ ተከትለን ራዕያቸውን እውን እናደርጋለን፡፡ ግድቡ የዚህ ዘመን ትልቁ ስጦታችን ነው»* እያለ ይነግራቸዋል፡፡ ጎብኚዎቹም በትኩረትና በጥሞና ይሰሙታል፡፡ ኤንጂነር ስመኘው ቀጠለ *«የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ግድብ መጠበቅ የሚችል በትልቅነቱ እስካሁን ድረስ በዓለም ፈፅሞ ያልተፈበረከ የኑክሌር ቦምብ ነው፡፡ ግድቡን እንደ ዓይን ብሌኑ ያየዋል፣ ይጠብቀዋል፣ ከግብ ያደርሰዋል፡፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዚህ ግድብ ግንባታ ያልተሳተፈ ዜጋ የለም፡፡ ግድቡ የሁላችንም ዓርማ፣ መለያና ሰንደቅ ዓላማችን ነው»*፡፡ እውነት ብለዋል ኤንጅነሩ፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ብሄራዊ ዓርማችን ነው፡፡